“የመባዕ አነስተኛ ፋይናንስ ተቋም የአክሲዮን ማህር የተሻሻለ መመስረቻ ጽሑፍ

ታሕሳስ 11 ቀን 2018 ዓ.ም

ማውጫ

መግቢያ.....1

ምዕራፍ አንድ.....1

ጠቅላላ ድንጋጌዎች.....1

አንቀጽ አንድ: የማህበሩ ስያሜ.....1

አንቀጽ ሁለት: የማህበሩ ዋና መ/ቤት.....1

አንቀጽ ሶስት: የማህበሩ ባለአክሲዮኖች.....1

አንቀጽ አራት: የማህበሩ የንግድ ዓላማዎችና ተግባራት.....2

አንቀጽ አምስት: የማህበሩ ዋና ገንዘብ.....3

አንቀጽ ስድስት: የማህበሩ እና ባለአክሲዮኖች ኃላፊነት.....3

ምዕራፍ ሁለት.....3

ስለአክሲዮን እና የባለአክሲዮኖች መብትና ግዴታ.....3

አንቀጽ ሰባት: ስለአክሲዮን.....3

አንቀጽ ስምንት: ስለአክሲዮን አለመከፋፈል.....4

አንቀጽ ዘጠኝ: የባለአክሲዮኖች መዝገብ.....4

አንቀጽ አስር: አክሲዮን ስለማስተላለፍ.....5

አንቀጽ አስራ አንድ: መያዣ ወይም አላባ መብት ስለተያዙ አክሲዮኖች.....5

አንቀጽ አስራ ሁለት: ቀሪ ዋጋቸው ያልተከፈሉ አክሲዮኖች.....5

አንቀጽ አስራ ሶስት.....5

አንቀጽ አስራ አራት: የማኅበሩ የአደራጆች እና የፈራሚ ባለአክስዮኖች ጥቅም.....6

ምዕራፍ ሶስት.....6

የአክሲዮን ማህበሩ አስተዳደር.....6

አንቀጽ አስራ አምስት; የአክሲዮን ማህበሩ አስተዳደር አካላት.....6

አንቀጽ አስራ ስድስት: የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔዎች.....6

አንቀጽ አስራ ሰባት: የመደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ሥልጣን.....7

አንቀጽ አስራ ስምንት: የአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ሥልጣን.....7

አንቀጽ አስራ ዘጠኝ: የጠቅላላ ጉባዔ አጠራር.....7

አንቀጽ ሃያ: የጠቅላላ ጉባዔ አጀንዳዎች.....8

አንቀጽ ሃያ አንድ: የጠቅላላ ጉባኤ አመራር.....8

አንቀጽ ሀያ ሁለት: ምልዐተ ጉባዔ.....8
አንቀጽ ሃያ ሶስት: ስለ ድምጽ ብልጫ.....8
አንቀጽ ሃያ አራት: የድምጽ አሰጣጥ.....9
አንቀጽ ሃያ አምስት: የውክልና ስልጣን.....9
አንቀጽ ሃያ ስድስት: ቃለ-ጉባዔ.....9
አንቀጽ ሃያ ሰባት: የጉባዔው ተሳታፋዎች መመዝገቢያ ሰነድ.....9
አንቀጽ ሃያ ስምንት: የዳይሬክተሮች ቦርድ.....9
አንቀጽ ሀያ ዘጠኝ: የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የስራ ዘመን.....10
አንቀጽ ሰላሳ: የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ እና ምክትል ሰብሳቢ.....10
አንቀጽ ሰላሳ አንድ: የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን ስለመተካት.....10
አንቀጽ ሰላሳ ሁለት: የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን ስለመሻር.....10
አንቀጽ ሰላሳ ሶስት: የዳይሬክተሮች የሥራ ዋጋና አበል.....11
አንቀጽ ሰላሳ አራት: የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ስለሚገቡት ዋስትና.....11
አንቀጽ ሰላሳ አምስት: ዳይሬክተሮች ቦርድ ስብሰባ.....11
አንቀጽ ሰላሳ ስድስት: የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ኃላፊነትና ተጠያቂነት.....12
አንቀጽ ሰላሳ ስምንት: የማህበሩ ዋና ሥራ አስፈጻሚ.....14
አንቀጽ ሰላሳ ዘጠኝ: የማህበሩ ፀሐፊ.....16
አንቀጽ አርባ: ኦዲተሮች.....16
ምዕራፍ አራት.....17
ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች.....17
አንቀጽ አርባ አንድ: ስለ ማህበሩ ዓመታዊ ሪፖርት.....17
አንቀጽ አርባ ሁለት: የማህበሩ ሂሳብ ዓመት.....17
አንቀጽ አርባ ሶስት: ሕጋዊ የመጠባቂያ ገንዘብ.....17
አንቀጽ አርባ አራት: የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት.....18
አንቀጽ አርባ አምስት: ስለ ትርፍ አደላደልና አከፋፈል.....18
አንቀጽ አርባ ስድስት: ስለማህበሩ መፍረስ እና ሂሳብ ማጣራት.....18
አንቀጽ አርባ ሰባት: ማህበሩ የተቋቋመት ጊዜ.....18
አንቀፅ አርባ ስምንት: የግልግል ዳኞች.....19
አንቀጽ አርባ ዘጠኝ: መመስረቻ ጽሁፍ ስለማሻሻልና ተፈጻሚነት.....19

መግቢያ

መባዕ አነስተኛ ፋይናንስ ተቋም አክሲዮን ማህበር (ከዚህ በኋላ ማህበር በሚል የተጠቀሰው) ኢትዮጵያ የንግድ ህግ፣ አነስተኛ የፋይናንስ ስራ አዋጅ ቁጥር 626/2001 (አዋጅ ቁጥር 1164/2012 እንደተሻሻለው) ፣ ንግድ ምዝገባ እና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2000 እና አግባብነት ባላቸው የብሔራዊ ባንክ መመሪያዎች መሰረት ተቋቁሞ አነስተኛ የፋይናንስ ንግድ ሥራ በማከናወን ላይ ይገኛል፡፡

የአክሲዮን ማህበሩ መመስረቻ ጽሁፍ በማህበሩ የፈራሚዎች ጉባዔ መጋቢት 30 ቀን 2015 ዓ.ም ጸድቆ ለመጀመሪያ ጊዜ ስራ ላይ የዋለ ሲሆን በ2013 ዓ.ም በወጣው የኢትዮጵያ የንግድ ህግ መሰረት የመመስረቻ ጽሁፉን በማዘጋጀት ስራውን ሲመራ ቆይቷል፡፡

ሆኖም ግን በአሁን ጊዜ በሀገራችን የፋይናንስ ሴክተር ፈጣን የሆኑ የፖሊሲ እና የህግ ማዕቀፍ ለውጦች እየተከናወኑ የሚገኙ መሆኑ እና ማህበራችን ራሱን ከዚህ ተለዋዋጭ ሁኔታ ጋር ማዛመድ እና ማጠናከር ያለበት በመሆኑ እንዲሁም በገበያ ተወዳዳሪ ሆኖ እንዲቀጥል ለማስቻል እና ህጋዊ ተገፂነቱን ለማረጋገጥ ያሉትን ነባራዊ ለውጦች መሠረት በማድረግ መመስረቻ ጽሁፉን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ የማህበሩ ባለአክሲዮኖች ህዳር 11 ቀን 2018 ዓ.ም ባከናወኑት አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ይህን የተሻሻለ መመሥረቻ ጽሑፍ አጽድቀዋል፡፡

ምዕራፍ አንድ
ጠቅላላ ድንጋጌዎች

አንቀጽ አንድ: የማህበሩ ስያሜ

የማህበሩ ስም መባዕ አነስተኛ ፋይናንስ ተቋም አክሲዮን ማህበር ነው፡፡

አንቀጽ ሁለት: የማህበሩ ዋና መ/ቤት

2.1. የማህበሩ ዋና መስሪያ ቤት አዲስ አበባ ከተማ ይሆናል፡፡

2.2. ማህበሩ አግባብነት ባላቸው ህጎች መሠረት ኢትዮጵያ ውስጥ ቅርንጫፎችን ሊያቋቁም ይችላል፡፡

አንቀጽ ሶስት: የማህበሩ ባለአክሲዮኖች

የአክሲዮን ማህበሩ ባለአክሲዮኖች ስም፣ ዜግነት፣ አድራሻ እና እያንዳንዱ ባለአክሲዮን ማህበሩ ላይ ያለው የተፈረመ እና የተከፈለ አክሲዮን መጠን ከዚህ መመስረቻ ጽሁፍ ጋር በተያያዘው ሰንጠረዥ ላይ የተገለጸው ነው፡፡

ተ.ቁ	የባለአክሲዮኑ ሙሉ ስም	ዜግነት	ክልል	ከተማ	ክ/ከተማ	ወረዳ/ቀሌ	ስልክ ቁጥር	የአንድ አክሲዮን ዋጋ	የተፈረመ አክሲዮን		የተከፈለ አክሲዮን		የአክሲዮን መዝገብ ላይ የተመዘገበበት ቀን
									የአክሲዮን ብዛት	የአክሲዮን መጠን (ገንዘብ)	የአክሲዮን ብዛት	የአክሲዮን መጠን (ገንዘብ)	
1													
2													

3													
4													
5													
6													
7													
8													
9													
ድምር													

<u>አንቀጽ አራት: የማህበሩ የንግድ ዓላማዎችና ተግባራት</u>

አነስተኛ ፋይናንስ ስራ አዋጅ ቁጥር 626/2001 (አዋጅ ቁጥር 1164/2012 እንደተሻሻለው) መሰረት ማይክሮ ፋይናንሱ የሚከተሉት የሥራ ዓላማዎችና ተግባሮች ይኖሩታል፣

4.1. ገንዘብ መሰብሰብ እና ገጠር እና ከተማ ግብርና ጥቃቅንና አነስተኛ የስራ መስኮች እንዲሁም ሌሎች መሰል ስራዎች ለተሰማሩ ሰዎች ጣሪያውን ብሔራዊ ባንክ የሚወስነውን ብድር መስጠት፤

4.2. የውዴታም ሆነ ግዴታ ቁጠባ በተጠየቀ ጊዜ የሚከፈል እንዲሁም የጊዜ ገደብ ተቀማጭ መቀበል፤

4.3. በገጠር እና ከተማ ግብርናና ሌሎች ስራዎች እንዲሁም ገጠርና ከተማ ጥቃቅንና አነስተኛ የስራ መስኮች ለተሰማሩ ሰዎች ብድር መስጠት፤

4.4. በኢትዮጵያ ውስጥ የሚከፈል የሃዋላ ሰነዶችን ማውጣት እና መቀበል፤

4.5. ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት አነስተኛ የመድህን ስራ መስራት፤

4.6. ዓላማቸው ገቢ ማስገኘት የሆነ እንደ ግምጃ ቤት ሰነዶችን እና ሌሎች የአጭር ጊዜ የንግድ ወረቀቶችን ብሔራዊ ባንክ በሚወስነው መሰረት መግዛት እና መሸጥ፤

4.7. ስራውን የሚያከናውንባቸውን ህንጻዎች ጨምሮ ማንኛውንም የሚንቀሳቀስ እና የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነት መያዝ መንከባከብ እና ለሌሎች ማስተላለፍ፤

4.8. በከተማና በገጠር ጥቃቅንና አነስተኛ የስራ መስኮች ወይም ሌላ ምርታማ ተግባራት የተሰማሩ ሰዎች የሚያካሂዷቸውን ገቢ የሚያስገኙ ፕሮጀክቶች ማገዝ፤

4.9. ለደንበኞች የአመራር፣ የገበያ፣ የቴክኒክና አስተዳደራዊ ምክር መስጠት እና በእነዚህም መስኮች አገልግሎት ማግኘት እንዲችሉ ማገዝ፤

4.10. ለጥቃቅንና አነስተኛ የንግድ ስራዎች ወይም ለሌላ ተያያዥ ምርታማ ስራዎች ዓላማ የሚውል ገንዘብ ማስተዳደር፤

4.11. የሀገር ውስጥ ሀዋላ አገልግሎት መስጠት፤

4.12. የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ኪራይ አገልግሎት ካፒታል እቃ ኪራይ ንግድ ስራ አዋጅ ቁጥር 103/1990 (አዋጅ ቁጥር 807/2005 እንደተሻሻለው) መሰረት ለአርሶ አደሮች እንዲሁም በገጠርና በከተማ ጥቃቅንና አነስተኛ የስራ መስኮች ለተሰማሩ ሰዎች መስጠት፤

4.13. የዲጂታል ፋይናንስ አገልግሎት መስጠት፤

4.14. የወኪል ባንኪንግ አገልግሎት መስጠት፣

4.15. ከወለድ ነጻ አነስተኛ የፋይናንስ ሥራ አገልግሎት መስጠት፤ እና

4.16. ሌሎች አግባብነት ያላቸው ሕጎችና ብሔራዊ ባንክ በየጊዜው በሚያወጣቸው መመሪያዎች በሚወሰኑ ሌሎች ስራዎች ላይ መሰማራት፡ ፡

አንቀጽ አምስት: የማህበሩ ዋና ገንዘብ

5.1. የማህበሩ የተፈረመ ዋና ገንዘብ ብር ብር 17,194,000 (አስራ ሰባት ሚሊዮን አንድ መቶ ዘጠና አራት ሺህ) ነው፡፡

5.2. የማህበሩ የተከፈለ ዋና ገንዘብ 17,194,000 (አስራ ሰባት ሚሊዮን አንድ መቶ ዘጠና አራት ሺህ) ሲሆን የእያንዳንዳቸው ዋጋ ብር 500.00 (አምስት መቶ) የተመዘገቡና ተራ አክሲዮኖች የተከፋፈለ ነው፡፡

5.3. የማኅበሩ ዋና ገንዘብ በባለአክስዮኖች ስም በተመዘገቡ 34,388 (ሰላሳ አራት ሺህ ሶስት መቶ ሰማንያ ስምንት) ተራ አክስዮኖች የተከፋፈለ ነው፡፡

አንቀጽ ስድስት: የማህበሩ እና ባለአክሲዮኖች ኃላፊነት እና ተጠያቂነት

6.1. የማህበሩ ባለአክሲዮኖች ኃላፊነት

6.1.1 የማህበሩ ኃላፊነት ማህበሩ ባለው ሀብት መጠን ልክ የተወሰነ ነው፡፡

6.1.2 ባለአክስዮኖች የማኅበሩ የተፈረሙ አክስዮኖች ዋጋ ሙሉ ለሙሉ ስለመከፈሉ ይከታተላሉ።

6.1.3 በንግድ ህግ የተቀመጡ ልዩ ሁኔታዎች እንደተጠቁ ሆነው የማህበሩ ባለአክሲዮኖች ኃላፊነት በንግድ ሕግ አንቀጽ 245(1) በተጠቀሰው መሰረት ለማህበሩ ቃል የገቡትን አክሲዮን በመክፈል የተወሰነ ነው፡፡

6.2 የማህበሩ ባለአክሲዮኖች ተጠያቂነት

6.2.1 የማኅበሩን፣ የባለአክስዮኖችን ወይም የማኅበሩን ገንዘብ ጠያቂዎችን ጥቅም ጉዳት ላይ የሚጥል ህገ-ወጥ ድርጊት ሆን ብሎ መፈፀም፣

6.2.2 የማኅበሩን ንብረት ከባለአክስዮኑ ንብረት ጋር መቀላቀል፣

6.2.3 የማኅበሩን እና የባለአክስዮኑን ማንነት አለመነጣጠል፣ ማኅበሩን ለግል ወይም ለሶስተኛ ወገን ዓላማና ጥቅም እንደ ሽፋን መጠቀም፣

6.2.4 ስለማኅበሩ የፋይናንስ አቋም የማኅበሩ ገንዘብ ጠያቂዎችን ሊያሳስት የሚችል መረጃ ሆን ብሎ ማውጣት፣

6.2.5 ከገበያ ዋጋ ባነሰ ክፍያ ወይም አግባብ ካለው የማኅበሩ አመራር ውሣኔ እና እውቅና ውጪ የማኅበሩን ሀብት ለራሱ ወይም ለሶስተኛ ወገኖች የግል ጥቅም ማዋል ወይም

6.2.6 በሕግ ከሚፈቀደው በላይ የትርፍ ክፍያ መፈፀም፡፡

ምዕራፍ ሁለት

ስለአክሲዮን እና የባለአክሲዮኖች መብትና ግዴታ

አንቀጽ ሰባት: ስለአክሲዮን

7.1. አክሲዮኖች ከተፃፈባቸው ዋጋ ሚበልጥ ዋጋ ሊወጡ ይችላሉ፡፡

7.2. አክሲዮኖች ከተጻፈባቸው ዋጋ ባነሰ ዋጋ ሊወጡ አይችሉም፡፡

7.3. የማህበሩ አክሲዮኖች ባለክሲዮኑ ስም የተመዘገቡ፣ ተራ እና እኩል ዋጋ ያላቸው አክሲዮኖች ናቸው፡፡

አንቀጽ ስምንት: ስለአክሲዮን አለመከፋፈል

8.1. አክሲዮን አይከፋፈልም፡፡

8.2. ከአንድ ላይ የሆኑ ባለአክሲዮኖች ጋራ የማህበሩ አክሲዮን ባለቤት መሆን ይችላሉ፡፡

8.3. የጋራ ባለአክሲዮኖች የባለአክሲዮን መብታቸውን ለመጠቀም የሚችሉት የጋራ ወኪል በመሾም ነው፡፡ የጋራ ወኪል ባልሾሙ ጊዜ ማህበሩ ለአንዱ ባለአክሲዮን የሰጠው ማስታወቂያ ወይም መግለጫ ለቀሪዎቹ ባለአክሲዮኖችም እንደተሰጠ ይቆጠራል፡፡

8.4. የጋራ ባለቤቶች ከባለአክሲዮንነት ለሚመነጩ ኃላፊነቶች አንድነት እና ነጠላ ተጠያቂ ናቸው፡፡

አንቀጽ ዘጠኝ: የባለአክሲዮኖች መዝገብ

9.1. የማህበሩ አክሲዮኖች አግባብነት ባላቸው የካፒታል ገበያ ባለስልጣን ሕግና መመሪያዎች መሠረት ማዕከላዊ የሠነደ ሙዓለ ነዋይ ግምጃ ቤት ይመዘገባሉ፡፡ ማህበሩ ዋና መስሪያ ቤት የሚቀመጥ እና ማዕከላዊ የሠነደ ሙዓለ ነዋይ ግምጃ ቤት ከተመዘገው መረጃ ጋር ተመሳሳይ የሆነ የባለአክሲዮኖች መዝገብ ኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ይይዛል፡፡

9.2. መዝገቡ የባለአክሲዮኖችን ስም፣ መለያ ቁጥር፣ የተፈረመና የተከፈለ አክሲዮን ብዛት፣ ዜግነት፣ አድራሻ፣ ባለአክሲዮኖቹ የተመዘገቡበትን ቀን እና ሌሎች አስፈላጊ ወይም ህግ የሚጠየቁ ጉዳዮችን መያዝ ይኖርታል፡፡

9.3. የማህበሩ ባለአክሲዮኖች ያለምንም ክፍያ መዝገቡን ለመመርመር ከውስጡም ቅጂዎችን ለመውሰድ ይችላሉ፡፡ ሌሎች ህግ የተፈቀደላቸው ሰዎች ማህበሩ የሚወስነውን ክፍያ በመክፈል መዝገቡን ሊመለከቱ ወይም ከውስጡም ቅጂዎችን ለመውሰድ ይችላሉ፡ ፡

9.4. መዝገቡን በማህበሩ መደበኛ የሥራ ሰዓት በማንኛውም ባለአክሲዮንና መዝገቡን ለመመርመር ሥልጣን በተሰጠው አካል ሊታይ በሚችልበት ሁኔታ በማኅበሩ ዋና ጽ/ቤት ወይም ዐቢይ ስራው በሚከናወንበት ቦታ ክፍት ሆኖ መቀመጥ አለበት፡፡

9.5. የአክሲዮን ባለቤቶች መዝገብ በግልጽ ለገበያ የቀረቡትና ግዑዝ አልባ የተደረጉትን ሁሉም የማኅበሩ አክሲዮኖች የመጨረሻው ትክክለኛ የባለቤትነት መዝገብ በካፒታል ገበያ አዋጅ፤ ለሕዝብ የሚሸጡ ሠነደ ሙዓለ ንዋዮችን ግዑዝ አልባ የማድረግ መመሪያና ሌሎች አግባብነት ባላቸው የካፒታል ገበያ ሕጎችና መመሪያዎች መሠረት በማዕከላዊ የሰነድ ሙዓለ ንዋይ ግምጃ ቤት ዘንድ የውስጥ መዝገቦችን ይይዛል፡፡

9.6. በማኅበሩ የውስጥ መዝገቦች ላይ የሚታወቅ ማንኛውም ስህተት ወይም ማዓከላዊ የሠነደ ሙዓለ ነዋዮች ግምጃ ቤት መመዝገብ ላይ ሪፖርት የተደረገ ማንኛውም ስህተት በመርመር ያስተካከላል፡፡ የማኅበሩ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ወይም አግባብነት ያለው ኃላፊ ስህተቱ ከተገኘ ወይም ከታወቀበት ጊዜ አንስቶ በሰላሳ (30) ቀናት ውስጥ እንደ አስፈላጊነቱ ከማዕከላዊ ሙዓለ ንዋዮች ግምጃ ቤት ጋር በመተባበር መመርመርና ማስተካከሉን ያረጋግጣል፡፡

9.7. የማኅበሩ የውስጥ አክስዮን ባለቤቶች መዝገብ አግባብነት ባለላቸው ሕጎች መሰረት የተፈቀደላቸው ሰዎች ምርመራ ክፍት ይሆናሉ፡፡

9.8. የማዕከላዊ የሠነደ ሙዓለ ንዋዮች መዝገብን የመመልከት ጉዳይ በግምጃ ቤቱ የአሰራር ደንቦች እና አግባብነት ባላቸው የካፒታል ሕጎች ይገዛል፡፡

አንቀጽ አስር: አክሲዮን ስለማስተላለፍ

10.1. የማህበሩ አክሲዮኖች ያለምንም ገደብ ከአንድ ሰው ወደ ሌላ ሰው ሊተላለፉ ይችላሉ፡፡

10.2. እንደነገሩ ሁኔታ አክሲዮኖች የሚተላለፉት መንገድ ሽያጭ፣ ስጦታ፣ ውርስ፣ ፍ/ቤት ትዕዛዝ ወይም ሌላ ህጋዊ ተቀባይት ባለው መንገድ ሊሆን ይችላል፡፡

10.3. አክሲዮን መዝገብ ያልተመዘገ የአክሲዮን ዝውውር ዋጋ የለውም፡፡

10.4. ማኅበሩ አክሲዮኖችን ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ከማኅበሩ ውጪ ለሚገኙ እና የማኅበሩ አካል መሆን ለሚፈልጉ ማህበር፣ ድርጅት አልያም ግለሰብ የኢትዮጲያ ካፒታል ገበያ በሚፈቅደው መንገድ አክሲዮኑ የሚተላለፍ ይሆናል፡፡

10.5. ለሕዝብ የሚሸጡ ሰንድ መዋለ ንዋዮችን ግዑዝ አልባ የማድረግ መመሪያ ቁጥር 1047/2017 አንቀጽ 5(3) ላይ የግዑዝ-ዐልባ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ባለቤትነት ዝውውር የሚደረገው በማዕከላዊ የሰነደ ንዋዮች ግምጃ ቤት ውስጥ የሚደረግ የኤሌክትሮኒክስ የምዝገባ ደብተር አማካኝነት የሚደረግ ይሆናል፡፡

10.6. የማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ የአክሲዮን ዝውውር አፈጻጸምን ተመለከተ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡

አንቀጽ አስራ አንድ: መያዣ ወይም አላባ ሙብት ስለተያዙ አክሲዮኖች

11.1. የማህበሩን አክሲዮኖች መያዣ ወይም አላባ ሙብት የያዙ ሰዎች ማህበሩ የአክሲዮን መዝገብ ላይ ማስመዝገብ አለባቸው፡፡

11.2. የማህበሩን አክሲዮኖች መያዣ ወይም አላባ የያዙ ሰዎች ያሏቸውን መብቶች እና ግዴታዎች በተመለከተ የንግድ ህግ አንቀጽ 271 ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

አንቀጽ አስራ ሁለት: ቀሪ ዋጋቸው ያልተከፈሉ አክሲዮኖች

12.1. በኩባንያው ውስጥ የአክሲዮን ሽያጭ ሁሉ ከኢትዮጲያ ንግድ ኮድ፣ ከካፒታል ሕግ፣ እና ከኢትዮጲያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣን እና ኢትዮጲያ የአክስዮን ገበያ መመሪያዎች በተያያዘ ይፈጸማል፡፡

12.2. በህግ የተቀመጠው ገደብ እንደተጠበቀ ሆኖ የአክሲዮን ባለይዞታዎች፣ አክሲዮኑ ቀደም ሲል ተላለፎላቸው የነበረ ሰዎች እንዲሁም አክሲዮኑን ከማህበሩ ለመግዛት የፈረሙ ሰዎች ቀሪ ዋጋቸው ላልተከፈለ አክሲዮኖች ዋጋ ለማህበሩ አንድነትና ተናጠል ኃላፊ ናቸው።

12.3. ቀሪ ዋጋቸው ያልተከፈለ አክሲዮኖችን ለማስከፈል ማህበሩ መከተል ያለበትን ሂደት ተመለከተ የንግድ ህግ አንቀጽ 289 ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

አንቀጽ አስራ ሶስት: የባለአክሲዮኖች ሙብቶች

በህግ የተቀመጡ ሙብቶች እንደተጠበቁ ሆነው እያንዳንዱ የማህበሩ ባለአክሲዮን የሚከተሉት ሙብቶች ይኖሩታል፡-

13.1. ባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔዎች ላይ መገኘት የመሳተፍ እና ሃሳብ የመስጠት፤ የመቃወም፤ ድምፅ የመስጠት፤

13.2. ከተጣራው የማህበሩ ትርፍ እንዲሁም ማህበሩ ሲፈርስ ከሚቀረው የተጣራ ንብረት ከፈለው የአክሲዮን መጠን ድርሻ የማግኘት፤

13.3. የመምረጥ፤ በህግ በተቀመጠው መስፈርት መሠረት የማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ሆኖ የመመረጥ ፤

13.4. የባለአክሲዮንነት ድርሻን ማስተላለፍ፤

13.5. አግባብነት ባለው ሕግ መሰረት የአክሲዮን ምስክር ወረቀት የማግኘት፤

13.6. የማህበሩን ዋና ገንዘብ ለመጨመር ተጨማሪ አክሲዮኖች በሚወጡት ጊዜ ማህበሩ ውስጥ ባለው የአክሲዮን ድርሻ መጠን ቀደምትነት የመግዛት መብት የማግኘት፤

13.7. የማህበሩን የሂሳብ ሚዛን፣ የትርፍና ኪሳራ መግለጫዎች፣ የኦዲተር ሪፖርቶች፣ የዳይሬክተሮች ቦርድ ሪፖርቶች እና ውሳኔዎች፣ የጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔዎች፣ የባለአክሲዮኖች መዝገብ መመርመር እና ኮፒዎችን መውሰድ፤

አንቀጽ አስራ አራት: የማኅበሩ የአደራጆች እና የፈራሚ ባለአክስዮኖች ጥቅም

ንግድ ሕጉ ድንጋጌዎች ለባለአክስዮኖች የተደነገጉ ጥቅሞች እንደተጠቁ ሆኖ አደራጆች እና ፈራሚ ባለአክስዮኖች የሚከተሉትን ልዩ ጥቅሞች ያገኛሉ፡-

14.1. ገንዘባቸውን፣ ጊዜያቸውንና እውቀታቸውን መስዋዕት ማድረግ የማኅበሩን ምስረታ እውን ላደረጉት የአደራጆች ማኅበሩ ማትረፍ ከጀመረት ጊዜ ጀምሮ ላሉት 3 ዓመታት ከማኅበሩ የተጣራ ትርፍ ላይ 10 መቶ ተመድቦላቸዋል፡፡ አደራጅ ኮሚቴ የሚባሉት ንግድ ሕጉ አንቀጽ 248 ላይ ተገለጸው መልኩ ማኅበሩ እንዲመሠረት ያደረጉ ናቸው፡፡

14.2. የአደራጆችም ሆኑ ፈራሚ ባለአክስዮኖች ከላይ ባሉት ንዑሳን አንቀጾች ከተጠቀሱት ጥቅሞች ውጪ ሌላ ልዩ ጥቅም ከአክስዮን ማኅኑ አያገኙም፡፡

ምዕራፍ ሶስት
የአክሲዮን ማህበሩ አስተዳደር

አንቀጽ አስራ አምስት; የአክሲዮን ማህበሩ አስተዳደር አካላት

15.1. የአክሲዮን ማህበሩ አስተዳደር አካላት የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ
2. የዳይሬክተሮች ቦርድ
3. ዋና ሥራ አስፈጻሚ
4. የማህበሩ ጸሐፊ
5. ኦዲተሮች

15.2. ከላይ የተመለከቱት የማኅበሩ ዋና ዋና አካላት ስልጣንና ተግባር በማኅበሩ መመስረቻ ጽሑፍና በኢትዮጵያ ንግድ ሕግ መሠረት ይወሰናል፤

15.3. ማኅበሩ ለሥራው አካሄድ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ተጠሪነታቸው ለአስተዳደር አካላት የሆኑ ኮሚቴዎችን ሊያዋቅር ይችላል፣

አንቀጽ አስራ ስድስት: የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔዎች

16.1. የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ሁሉም ባለአክሲዮች የሚሳተፉት የማህበሩ ከፍተኛ ውሳኔ ሰጪ አካል ነው፡፡

16.2. የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔዎች ሁሉም የማህበሩ ባለአክሲዮኖች ላይ ተፈጻሚነት አላቸው፡፡

16.3. የማህበሩ ባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔዎች መደበኛ ወይም አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ናቸው፡፡

አንቀጽ አስራ ሰባት: የመደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ሥልጣን

በህግ የተሰጡት ስልጣኖች እንደተጠበቁ ሆኖ የማህበሩ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ የሚከተሉት ተጨማሪ ስልጣኖች አሉት፡፡

17.1. የማህበሩን የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን መሾም፣ መሻር፣ አል እና የስራ ዋጋቸውን መወሰን፤

17.2. የማህበሩን ኦዲተሮች መሾም፣ መሻር፣ ክፍያቸውንም መወሰን፤

17.3. የሂሳብ ሚዛን፣ የትርፍና ኪሳራ መግለጫ፣ እንዲሁም የቦርድንና የኦዲተሮችን ሪፖርቶች መርምሮ ተገቢውን ውሳኔ መስጠት፤

17.4. ትርፍ ድርሻ ክፍፍል እንዲሁም ካለፈው የሂሳብ ዓመት ጋር ተያይዘው የሚነሱ የሂሳብ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ መስጠት፤

17.5. ማህበሩ የግዴታ ወረቀቶችን እንዲያወጣ መፍቀድ፤

17.6. የማህበሩን ዳይሬክተሮች ቦርድ ጥቆማ እና ምርጫ አፈጻጸም ደንብ ማጽደቅ፤

17.7. የዳይሬክተሮች ቦርድ አስመራጭ ኮሚቴ፤ አባላትን ይሾማል፤ ይሽራል፣

17.8. ለአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ግልጽ ተለይተው ከተሰጡት ጉዳዮች በስተቀር ሌሎች የማህበሩ ጉዳዮች ሁሉ ላይ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

አንቀጽ አስራ ስምንት: የአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ሥልጣን

በህግ የተሰጡት ተጨማሪ ስልጣኖች እንደተጠበቁ ሆኖ የማህበሩ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ የሚከተሉት ስልጣኖች አሉት፡፡

18.1. የማህበሩን መመሥረቻ ፅሑፍ ማሻሻል፤

18.2. የማህበሩ ዋና ገንዘብ መጨመር ወይም መቀነስ፤

18.3. የማህበሩ ስም ወይም ዜግነት መለወጥ፤

18.4. ማህበሩ እንዲፈርስ፤ ወደ ሌላ ዓይነት የንግድ ማህበር እንዲለወጥ፣ እንዲከፈል፣ ሒሳቡ እንዲጣራ መወሰን ወይም ከሌላ ማህበር ጋር እንዲዋሐድ መወሰን፤

18.5. ሌሎች ሕግ ለአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ተለይተው የተሰጡ ጉዳዮች ላይ መወሰን፤

አንቀጽ አስራ ዘጠኝ: የጠቅላላ ጉባዔ አጠራር

19.1. የማህበሩ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ የሂሳብ ዓመቱ ከተጠናቀቀበት ቀን ጀምሮ ባሉት ስድስት ወራት ውስጥ መካሄድ አለበት፡፡ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ተጨማሪ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔዎች ማንኛውም ጊዜ ሊደረጉ ይችላሉ፡፡

19.2. የማህበሩ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ማናቸውም ጊዜ ሊጠራ ይችላል፡፡

19.3. የጠቅላላ ጉባዔ ጥሪ የሚያደርጉት እንደነገሩ ሁኔታ የዳይሬክተሮች ቦርድ፣ ኦዲተሮች፣ ሂሳብ አጣሪዎች፣ ፍርድ ቤት ወይም ሌሎች በህግ ሥልጣን የተሰጣቸው አካላት ናቸው።

19.4. የጠቅላላ ጉባዔ ጥሪ እንዲከናወን ከጉባዔው 24 ቀናት በፊት አገሪቱ ውስጥ በሚታተም አገር አቀፍ ስርጭት ባለው ጋዜጣ፣ ቴሌቪዥን፣ ራዲዮ፣ ማህራዊ ሚዲያ ወይም ሌላ የኤሌክትሮኒክስ መገናኛ ዘዴ መተላለፍ ይኖርታል፡፡

19.5. ምልዐተ ጉባዔ ባለመሟላቱ ጠቅላላ ጉባዔው መሰብሰብ ሳይችል የቀረ እንደሆነ ድጋሜ ጠቅላላ ጉባዔው እንዲሰበሰብ የሚደረገው ጥሪ የመጀመሪያው ጉባዔ ተጠራት አኳኋን እና ህግ ተቀመጠው የጊዜ ገደብ ይደረጋል፡፡

19.6. የጠቅላላ ጉባዔ የጥሪ ማስታወቂያ የማህበሩን ስምና ዓይነት፣ የማህበሩን ዋና ገንዘብ፣ የምዝገባ ቁጥር፤ ዋና መሥሪያ ቤቱ የሚገኝትን ቦታ፤ የስብሰባውን ጊዜና ቦታ እንዲሁም በስብሰባው የሚቀርቡ አጀንዳዎችን መያዝ አለበት።

አንቀጽ ሃያ: የጠቅላላ ጉባዔ አጀንዳዎች

20.1. የማህበሩን ጠቅላላ ጉባዔ አጀንዳ የሚያዘጋጀው ጥሪ አድራጊው አካል ነው።

20.2. የጉባኤው አጀንዳ ዝርዝር ጉባዔው ጥሪ ማስታወቂያ ላይ ይገለፃል፡፡

20.3. ዳይሬክተሮችን በሚመለከት ንግድ ሕጉ ቁጥር 372(3) የተመለከተው እንደተጠቀ ሆኖ ጉባኤው በሚካሄድት ጊዜ ጉባዔው ጥሪ ማስታወቂያ አስቀድሞ ከተገለጸው የአጀንዳ ዝርዝር ውጭ ሌላ ጉዳይ ለውይይትና ለውሳኔ ሊቀርብ አይችልም፡፡

20.4. የማህበሩ ባለአክሲዮኖች ንግድ በህጉ ተቀመጠው መስፈርት እና ሂደት መሠረት ተጨማሪ አጀንዳዎች እንዲያዙ መጠየቅ ይችላሉ፡፡

አንቀጽ ሃያ አንድ: የጠቅላላ ጉባኤ አመራር

21.1. በህግ የተቀመጠው ልዩ ሁኔታ እንደተጠበቀ ሆኖ የጠቅላላ ጉባኤዎች ሰብሳቢ የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ ነው፡፡ ሰብሳቢው በማይኖርት ጊዜ የቦርዱ ምክትል ሰብሳቢ ጉባዔውን ይመራል፡፡ምክትል ሰብሳቢውም የሌለ እንደሆነ ከዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት መካከል ሥራ ቀደምትነት ያለው ዳይሬክተር የጉባዔው ሰብሳቢ ይሆናል፡፡ ቀደምትነት ያለው ዳይሬክተር በማይኖርት ጊዜ የጉባዔው ሰብሳቢ ጠቅላላ ጉባዔው ይመረጣል፡፡

21.2. ማናቸውም ጉባኤ ከፍተኛ አክሲዮን /ድምፅ/ ባላቸው አባላት መካከል ሚደረግ ስምምነት ሁለት ፈቃደኛ የሆኑ ባለአክሲዮኖች የጉባኤው ድምፅ ቆጣሪዎች ሆነው ይሰየማሉ፡፡

አንቀጽ ሀያ ሁለት: ምልዐተ ጉባዔ

22.1. **መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ፡-**

ሀ) ለመደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ መጀመሪያ ጥሪ ድምፅ ለመስጠት መብት ካላቸው አክሲዮኖች የማህበሩን ዋና ገንዘብ አንድ አራተኛ (1/4ኛ) የሚወክሉ ባለአክሲዮኖች ወይም ወኪሎች መገኘት አለባቸው፡፡

ለ) ሁለተኛ ጥሪ ግን የተገኙት አክሲዮኖች ቁጥር ከግምት ሳይገባ ምልዓተ ጉባኤ እንዳለ ተቆጥሮ ጉባኤው ይደረጋል፡፡

22.2. **አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ፡-**

ሀ) ለአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ መጀመሪያው ጥሪ ድምፅ ለመስጠት መብት ካላቸው አክሲዮኖች ውስጥ ቢያንስ የማህበሩን ዋና ገንዘብ አንድ ሶስተኛ (1/3ኛ) የሚወክሉ ባለአክሲዮኖች ወይም ወኪሎቻቸው መገኘት አለባቸው፡፡

ለ) ሁለተኛው ጥሪ ቢያንስ የማህበሩን ዋና ገንዘብ አንድ አራተኛ (1/4ኛ) የሚወክሉ ባለአክሲዮኖች ወይም ወኪሎቻቸው መገኘት ሲኖርባቸው ሦስተኛው ጥሪ ግን የተገኙት አክሲዮኖች ቁጥር ከግምት ውስጥ ሳይገባ ምልዓተ ጉባዔ እንደተሟላ ተቆጥሮ ጉባዔው ይከናወናል፡፡

አንቀጽ ሃያ ሶስት: ስለ ድምጽ ብልጫ

23.1. የመደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔዎች የሚተላለፉት በጉባዔው ከተገኙት ድምጽ የመስጠት መብት ካላቸው አክሲዮኖች አብላጫውን ዋና ገንዘብ በሚወክሉት ድምጽ ከተደገፈ ነው፡፡

23.2. የአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔ የጸና የሚሆነው ጉባዔው የተገኙትና ድምጽ የመስጠት መብት ካላቸው አክሲዮኖች ከወከሉት ዋና ገንዘብ ሁለት ሶስተኛውን (2/3ኛ) በሚወክሉት ድምጽ ከተደገፈ ነው፡፡

23.3. በንዑስ አንቀጽ 23.2 የተመለከተው ቢኖርም የማህበሩን ዜግነት ለመለወጥ እና ነባር አክሲዮኖች ላይ ዋጋ መጨመር የማህበሩን ዋና ገንዘብ ለመጨመር የባለአክሲዮኖች ሙሉ ድጋፍ ያስፈልጋል፡፡

23.4. ለድምጽ ብልጫ አቆጣጠር ስሌት ድምጽ ያልሰጡና ያልተጻፈባቸው የድምጽ መስጫ ወረቀቶች ግምት ውስጥ አይገቡም፡፡

አንቀጽ ሃያ አራት: የድምጽ አሰጣጥ

24.1. እያንዳንዱ አክሲዮን አንድ ድምጽ ይኖረዋል፡፡

24.2. ማንኛውም ባለአክሲዮን ስለራሱ ወይም ሦስተኛ ወገንን መወከል ከማህበሩ ጋር የጥቅም ግጭት በሚያስነሱ አጀንዳዎች ላይ ድምፅ መስጠት አይችልም።

24.3. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የራሳቸውን ሀላፊነት፣ ተጠያቂነት እንዲሁም ከማህበሩ ጋር ቀጥታም ሆነ ተዘዋዋሪ የጥቅም ግጭት በሚያስነሱ አጀንዳዎች ላይ ድምፅ መስጠት አይችሉም።

አንቀጽ ሃያ አምስት: የውክልና ስልጣን

25.1. ማንኛውም ባለአክሲዮን ማህበሩ ጉባዔዎች ላይ ባለአክሲዮን በሆነ ወይም ባልሆነ ሌላ ሰው ሊወከል ይችላል፡፡ የውክልና ሥልጣን የሰጠ ባለአክሲዮን እራሱ ጉባዔው ላይ መሳተፍና ድምጽ መስጠት አይችልም፡፡

25.2. ጠቅላላ ጉባዔ ለመሳተፍ የሚሰጠው የውክልና ስልጣን በጽሁፍ መሆን እና መፈረም ይኖርታል፡፡ የውክልና ሥልጣን መስጫ ቅጹ ይዘት፣ ውክልናው የሚቀመጥት ቦታና ጊዜ ማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ይወሰናል፡፡ ይህ በባለአክሲዮኖች ጉባዔ ለመሳተፍ የሚሰጥ ውክልና ከአንድ ጉባኤ ላይ አያገለግልም፡፡

25.3. ጉባኤው ውክልና የተገኘው ሰው ሙብትና ግዴታውን በሚመለከት እንደ ወካዩ ባለአክሲዮን ይቆጠራል፡፡

አንቀጽ ሃያ ስድስት: ቃለ-ጉባዔ

26.1. የማህበሩ ጠቅላላ ጉባዔ ውይይት እና ውሳኔ ቃለ ጉባዔ መያዝ አለበት፡፡ ቃለ ጉባዔው ንግድ ህጉ አንቀጽ 387 (3) የተመለከቱትን ዝርዝር ጉዳዮች መያዝ አለበት፡፡

26.2. በንግድ ህጉ አንቀጽ 387 (2) መሠረት ለጉባዔው የተሰጠው ስልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ ጉባዔው ላይ የተደረገው ውይይት እና የተላለፈው ውሳኔ ትክክል ቃለ ጉባዔ መገልበጡ ጉባዔው ላይ ተገኙት በማህበሩ ዳይሬክተሮች እና በማህበሩ ጸሐፊ መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

አንቀጽ ሃያ ሰባት: የጉባዔው ተሳታፉዎች መመዝገቢያ ሰነድ

27.1. ማህበሩ ንግድ ሕጉ አንቀጽ 378 መሠረት ጉባኤው ላይ የተገኙትን ተሳታፊዎች መመዝገቢያ ሰነድ መያዝ አለበት፡፡

27.2. መመዝገቢያ ሰነዱ ንግድ ህግ አንቀጽ 378 (1) ላይ የተመለከቱትን ጉዳዮች መያዝ ያለበት ሲሆን ጉባዔው አካል የተገኙ ባለአክሲዮኖች ወይም ወኪሎች የፈረሙት ስለመሆኑ ማህበሩ ፀሐፊ መረጋገጥ ይኖርታል፡፡

አንቀጽ ሃያ ስምንት: የዳይሬክተሮች ቦርድ

28.1. ማህበሩ ባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ የሚሾሙ ዘጠኝ (9) አባላት ባሉት የዳይሬክተሮች ቦርድ ይመራል፡፡

28.2. ከማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት መካከል ሶስቱ (3) ህግ የተቀመጠውን መስፈርት የሚያሟሉ ገለልተኛ ዳይሬክተሮች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

28.3. የማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ብሔራዊ ባንክ የተቀመጡ መስፈርቶች መሰረት ተገቢውን የትምህርት፣ የስራ ልምድና የጾታ ስብጥርን ያሟላ መሆን ይኖርበታል፡፡ የቦርድ አባል ሆነው መመረጥ የሚችሉት አግባብነት ባላቸው ህጎች መሠረት አስፈላጊውን የብቃት እና የተገቢነት መስፈርት የሚያሟሉ ናቸው፡፡

28.4. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ማህበሩን አንድነት ይወክላሉ፡፡

አንቀጽ ሀያ ዘጠኝ: የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የስራ ዘመን

29.1. የማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የሥራ ዘመን ሶስት (3) ዓመት ነው፡፡ የስራ ዘመናቸው የተጠናቀቀ ዳይሬክተሮች ለሁለተኛ (2) ጊዜ ድጋሚ መመረጥ ይችላሉ፡፡ ዳይሬክተሮች በልዩ ሁኔታ ለሶስተኛ (3ኛ) ጊዜ ሊመረጡ ይችላሉ፡፡

29.2. ንዑስ አንቀጽ አንድ የተቀመጠው ቢኖርም አዲስ የተሾሙት ዳይሬክተሮች ሹመት ብሔራዊ ባንክ እስከሚጸድቅ ድረስ የስራ ዘመናቸው የተጠናቀቀ ዳይሬክተሮች ስራ ላይ ይቆያሉ፡፡

አንቀጽ ሰላሳ: የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ እና ምክትል ሰብሳቢ

30.1. የማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢና ምክትል ሰብሳቢ በዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ይመረጣሉ፡፡ የቦርዱ ሰብሳቢ መሆን የሚችለው የማህበሩ ባለአክሲዮን የሆነ የቦርድ አባል ብቻ ነው፡፡

30.2. የማህበሩ ቦርድ ሰብሳቢውን ወይም ምክትል ሰብሳቢውን ማንኛውም ጊዜ መሻር በምትካቸው ሌላ ሰብሳቢ ወይም ምክትል ሰብሳቢ መሾም ይችላል፡፡

አንቀጽ ሰላሳ አንድ: የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን ስለመተካት

31.1. ሂሳብ ዓመቱ አንድ ወይም ከዚያ ላይ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የጎደሉ እንደሆነ የቀሩት አባላት ከግማሽ በላይ ከሆኑ የጎደሉት ምትክ ከተጠባባቂ ዳይሬክተሮች መካከል ይተካሉ፡፡

31.2. የተተኪ ዳይሬክተሮች ሹመት አንዲጸድቅ የሚቀጥለው ጠቅላላ ጉባዔ መቅረብ አለበት፡፡ ጉባዔው ሹመቱን ሊያፀድቅ ወይም በምትካቸው ሌሎች ዳይሬክተሮችን መሾም ይችላል፡፡

31.3. የተተኪዎቹ ዳይሬክተሮች የሥራ ዘመን የሚያቃው የጎደሉት አባላት የሥራ ዘመን በሚያቃት ጊዜ ነው፡፡

31.4. የቀሩት የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ቁጥር ከጠቅላላው የአባላት ቁጥር ከግማሽ በታች ከሆነ የቀሩት አባላት የጎደሉትን ለመሙላት መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ መጥራት አለባቸው፡፡

አንቀጽ ሰላሳ ሁለት: የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን ስለመሻር

32.1. የማህበሩ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ በማንኛውም ጊዜ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን መሻር ይችላል፡፡

32.2. ንዑስ አንቀጽ 1 የተቀመጠው እንደተጠቀ ሆኖ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ሚከተሉት ምክንያቶች ሊሻር ይችላል፡-

32.2.1. በህግ የተቀመጡ መስፈርቶችን ወይም የሥነ ስርዐት ደንቦችን መጣስ የተመረጠ መሆኑ ሲረጋገጥ፤

32.2.2. ኃላፊነቱን በአግባቡ አንዳይወጣ የሚያደርግ የተረጋገጠ የጤና ችግር ሲያጋጥመው፤

32.2.3. እምነት በማጉደል፣ ሙስና፣ ለመልካም ጸባይ ተቃራኒ ሆነ ወይም ሌላ ማንኛውም ተመሳሳይ ወንጀል ተከሶ ጥፋተኛ መሆኑ ሲረጋገጥ፤

32.2.4. በማንኛውም ወንጀል ከስድስት ወር የሚልጥ የእስራት ቅጣት ተፈርዶበት ወደ ማረሚያ ቤት ሲላክ፤

32.2.5. በበጀት ዓመቱ ከተከናወኑ የቦርድ ስብሰባዎች ቢያንስ 75 በመቶውን ያለ በቂ ምክንያት አካል ያልተሳተፈ፤

32.2.6. እያወቀ ከማህበሩ ጋር የጥቅም ግጭት የሚፈጥር ተግባር ሲፈጽም፤

32.2.7. በህግ ሰውነት የተሰጠው አካል ከሆነ ሲከስር፤

32.2.8. በህግ ተቀመጡ ወይም መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔው በቂ ናቸው ብሎ ባመነባቸው ሌሎች ምክንያቶች፤

32.3. ንዑስ አንቀጽ 32.2 መሠረት አንድን የቦርድ አባል ለመሻር በቂ የሆኑ ምክንያቶች በሚከሰቱበት ወቅት የቦርድ አባሉ ከኃላፊነቱ እንዲሻር የዳይሬክተሮች ቦርድ ለባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፡፡

አንቀጽ ሰላሳ ሶስት: የዳይሬክተሮች የሥራ ዋጋና አበል

33.1. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ለሚሰጡት አገልግሎት ማህበሩ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ የሚወሰን የሥራ ዋጋ ይከፈላቸዋል፡፡

33.2. ብሔራዊ ባንክ መመሪያ የተቀመጠው ገደብ እንደተጠቀ ሆኖ የማህበሩ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ለዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ሊከፈል የሚገባውን ከጠቅላላው ወጪ ላይ የሚታሰብ ዓመታዊ የሥራ ዋጋና አበል ይወስናል፡፡ በተጨማሪም በንግድ ህጉ እና ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት የተቀመጠው እንደተጠበቀ ሆኖ ጉባዔው ከማህበሩ ዓመታዊ የተጣራ ትርፍ ላይ የተወሰነ ድርሻ ለዳይሬክተሮች እንዲሰጥ ለመወሰን ይችላል፡፡

33.3. ከማህበሩ የተጣራ ትርፍ ላይ ለዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ክፍያ የሚፈጸመው በዚያው ዓመት ለባለአክሲዮኖች የትርፍ ድርሻ የተሰጠ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡ ለቦርድ አባላት የሚከፈለው የሥራ ዋጋ ወይም አበል አባሉ ዓመታዊ የቦርድ ስብሰባ ተሳትፎ ልክ የሚከፈል ይሆናል፡፡

አንቀጽ ሰላሳ አራት: የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ስለሚገቡት ዋስትና

34.1. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ለተጣለባቸው ተግባርና ኃላፊነት መልካም ስራ አፈጻጸም ዋስትና የሚሆኑ ጠቅላላ ዋጋቸው ብር 10,000.00 (አስር ሺህ) የሆነ 20 አክሲዮኖች እያንዳንዳቸው ማስያዝ ይኖርባቸዋል፡፡

34.2. የማህበሩ ባለአክሲዮን ያልሆኑ ዳይሬክተሮች ቀደም ሲል ከተጠቀሰው የዋስትና ገንዘብ መጠን ጋር ተመጣጣኝ የሆነና በህግ ተቀባይነት ያለው ማንኛውም ዋስትና ማስያዝ ይችላሉ፡፡

34.3. በዋስትና በማህበሩ የተያዙ እና የተቀመጡት አክሲዮኖች ወይም መያዣዎች የሚለቀቁት ዳይሬክተሩ ከኃላፊነቱ ሲለቅ እና ሥራ ላይ በነበረበት ጊዜ ከማህበሩ የሚፈለግት ዕዳ የሌለ መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡

አንቀጽ ሰላሳ አምስት: ዳይሬክተሮች ቦርድ ስብሰባ

35.1. ሌላ ጊዜ ወይም ቦታ እንዲሆን ካልተወሰነ ስተቀር የዳይሬክተሮች ቦርድ በማህበሩ ዋና መሥሪያ ቤት ወይም ኤሌክትሮኒክ ዘዴ ቢያንስ በወር አንዴ መደበኛ ስብሰባን ያደርጋል፡፡ የቦርዱ ሰብሳቢ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ተጨማሪ ስብሰባዎች ሊጠራ ይችላል፡፡

35.2. የቦርድ ስብሰባዎች የሚጠሩት ሰብሳቢው ወይም እሱ በማይኖርት ጊዜ ምክትል ሰብሳቢው ይሆናል፡፡ የጥሪ ማስታወቂያው ስብሰባው ከሚከናወንበት ቀን አስቀድሞ የስብሰባውን አጀንዳ ማያያዝ ለሁሉም ዳይሬክተሮች መላክ አለበት፡፡

35.3. የቦርድ ስብሰባ ቦርዱ ሰብሳቢ ወይም እሱ በማይኖርት ጊዜ ምክትል ሰብሳቢው ይመራል፡፡ ሁለቱም በማይኖሩት ጊዜ ስብሰባውን የሚመራው ዳይሬክተር በስብሰባው በተገኙት የቦርድ አባላት ይመረጣል፡፡

35.4. ምልዐተ ጉባዔ የሚሟላው ከአጠቃላይ የቦርድ አባላት ቢያንስ ግማሹ ሲገኙ ነው፡፡

35.5. የቦርድ ውሳኔዎች የሚተላለፉት በድምጽ ብልጫ ነው፡፡ እያንዳንዱ ዳይሬክተር አንድ ድምጽ ይኖረዋል፡፡ የተሰጠው ድምጽ እኩል ለእኩል በሚሆንት ጊዜ የቦርዱ ሰብሳቢ ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፡፡

35.6. የቦርድ ስብሰባዎች ላይ አንድ የቦርድ አባል በሌላ የቦርድ አባል ሊወከል ይችላል፡፡ ሆኖም ግን ማንኛውም የቦርድ አባል ከአንድ በላይ ለሆኑ የቦርድ አባላት ተወካይ መሆን አይችልም፡፡

35.7. የቦርድ ስብሰባዎች ቃለ ጉባዔ ተይዘው ስብሰባው በተገኙ ዳይሬክተሮች እና ማህበሩ ጸሐፊ መፈረም አለባቸው፡፡

35.8. ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ሥነ ስርዓት ደንብ ያወጣል፡፡ ሁሉም ዳይሬክተሮች ለዚህ መተዳደሪያ ደንብ ተገዢ መሆን አለባቸው፡፡

<u>አንቀጽ ሰላሳ ስድስት: የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ኃላፊነትና ተጠያቂነት</u>

በንግድ ሕጉ እና ብሔራዊ ባንክ መመሪያ የተጠቀሰው እንደተጠቀ ሆኖ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ከዚህ ቀጥሎ የተመለከቱት ኃላፊነቶችና ተጠያቂነት ይኖርባቸዋል፡፡

36.1. የማህበሩ ቦርድ አባላት ማህበሩን እና ሁሉንም የማህበሩ ባለአክሲዮኖች ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ መሥራት ይኖርባቸዋል፡፡

36.2. በህግ የተቀመጠው እንደተጠቀ ሆኖ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ኃላፊነታቸውን ቅን ልቦና፣ ጥንቃቄ እና ትጋት የመፈጸም ግዴታ አለባቸው፡፡

36.3. ማንኛውም የቦርድ አባል ከማህበሩ ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የጥቅም ግጭት ሊፈጥሩ ከሚችሉ ሁኔታዎች ራሱን ማራቅ ይኖርበታል፡፡

36.4. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ኃላፊነታቸውን ባለመወጣታቸው ለሚደርሰው ጉዳት ለማህበሩ አንድነትና ተናጠል ተጠያቂ ናቸው።

<u>አንቀጽ ሰላሳ ሰባት: የዳይሬክተሮች ቦርድ ሥልጣንና ተግባር</u>

የዳይሬክተሮች ቦርድ በሕግ፣ በማኅበሩ የመመስረቻ ፅሁፉ ወይም በጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔዎች የተሰጡትን ተግባራት የመፈፀም ግዴታ አለበት፤ ይህ ጠቅላላ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ቦርዱ የሚከተሉት ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

37.1. የማኅበሩን ፋይናንስ ያስተዳድራል፣ ማኅበሩ በቂ ዋና ገንዘብ እና ክፍያዎችን የመፈፀም አቅም ያለው መሆኑን ያረጋግጣል፣

37.2. ማይክሮፋይናንሱ የሚያደርገውን ኢንቨስትመንት ያጸድቃል፡፡

37.3. የማይክሮፋይናንሱን የአደጋ ተጋላጭነት እና ውስጣዊ አሰራር ለመቆጣጠር የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፡፡

37.4. የማይክሮፋይናንሱን መዋቅራዊ አደረጃጀት እና የሰራተኞች ደመወዝስኬልና ጥቅማ ጥቅም ያጸድቃል፡፡

37.5. የማይክሮፋይናንሱን ፖሊሲዎች ያጸድቃል፤ ያሻሽላል፡፡

37.1. የማኅበሩን የባንክ ሒሳብ የሚያንቀሳቅሱ ፈራሚዎችን እንደ አስፈላጊነቱ ይመድባል፤

37.2. የማይክሮ ፋይናንሱ የወለድ ምጣኔ ተመን ያፀድቃል፤ ያሻሽላል፡፡

37.3. የማይክሮ ፋይናንሱን ስትራቴጂክ ዕቅድ፣ አመታዊ ዕቅድና በጀት ያጸድቃል፤ አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፡፡

37.4. የማይክሮ ፋይናንሱን ዋና ስራ አስኪያጅ እና ምክትል ስራ አስኪያጆች ይሾማል፤ ከስራ ያሰናብታል፡፡

37.5. የማይክሮ ፋይናንሱ ዋና ስራ አስኪያጅ በሚያቀርበው የውሳኔ ሀሳብ መሠረት ቅርንጫፎችን ስለመክፈት እና መዝጋት፥ የመምሪያ ዳይሬክተሮች/ስራ አስኪያጆች እና የማይክሮ ፋይናንሱ ፀሐፊ ሹመት፣ ምደባና ስንብት ላይ ይወስናል፡፡

37.6. በእያንዳንዱ የሂሳብ ዓመት መጨረሻ የንብረት ቆጠራ ሥራዎች በወቅቱ በማከናወን የማይክሮ ፋይናንሱን ትርፍና ኪሳራ የሚያሳይ የሂሳብ ሚዛን መግለጫ ያዘጋጃል፡፡

37.7. የማይክሮፋይናንሱን የባለአክሲዮኖች ጉባኤ ይጠራል፣ የፋይናንስ እንቅስቃሴን ያካተተ አመታዊ የስራ አፈፃፀም ሪፖርት ለጉባዔው ያቀርባል፡፡

37.8. የጠቅላላ ጉባኤ እና የቦርድ ስብሰባዎች ቃለ ጉባኤ፣ የሒሳብ መዝገብ፣ የአክሲዮን መዝገብ፣ የዳይሬክተሮች መዝገብ እና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶች እንዲያዙ ያደርጋል፡፡

37.9. የማይክሮፋይናንሱን የውጭ ኦዲተሮች ሹመት እና የስራ ዋጋ እንዲፀድቅ ለመደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ያቀርባል፡፡

37.10. ለማይክሮፋይናንሱ ስራ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከባንክ እና ከሌሎች ተቋማት ብድር ለመበደር እና የማህበሩን የሚንቀሳቀስ፣ የማይንቀሳቀስ ንብረቶችን ለማህበሩ ወይም ለሶስተኛ ወገን ጥቅም በዋስትና ለመስጠት ከማይክሮፋይናንሱ ስራ አስኪያጅ የሚቀርብለትን የውሳኔ ሐሳብ መርመሮ እና ለማህበሩ ጥቅም አስፈላጊ መሆኑን ተመልክቶ ያፀድቃል፡፡

37.11. ለማይክሮፋይናንሱ ስራ ሒደት አስፈላጊ ሲሆን እና ከማሕበሩ ጋር ቅርብ ግንኙነት ላላቸው ሶስተኛ ወገኖች አስፈላጊ እና የማህበሩን ጥቅም የሚያስጠብቅ መሆኑን ሲያረጋግጥ በማህበሩ ስም የአንድነት እና የነጠላ ዋስትናን ለማህበሩ ወይም ለሶስተኛ ወገን ጥቅም በመያዣ መልክ እንዲሰጥ እንዲሁም ከባንኮችና ሌሎች የፋይናንስ ተቋማት ገንዘብ ለመበደር የሚቀርቡ የውሳኔ ሃሳቦችን ያፀድቃል፡ ፡

37.12. የግዴታ ወረቀቶችን ያወጣል ከዚያም ጋር የተያያዙትን ዋስትናዎች ያፀድቃል፡፡

37.13. የብሔራዊ ባንክ መመሪያ በሚፈቅደው መሰረት ብድር ነክ ያልሆኑ የማይክሮፋይናንሱን የማይንቀሳቀስና የሚንቀሳቀስ ንብረት ለመግዛት፣ ለመሸጥ፣ ለመለወጥ፣ ለማስወገድ እና ባለቤትነት ለማስተላለፍ ይወስናል፡፡

37.14. ለማይክሮፋይናንሱ ስራ አላማዎች ግብ መምታት አስፈላጊ የሆኑ ሕጋዊ እርምጃዎችን ይወስዳል፡፡

37.15. ገንቢ መስሎ የሚታየውን ማንኛውንም ሃሳብ ለባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ያቀርባል፡፡

37.16. በማይክሮፋይናንሱ ዋና ጽ/ቤት ወይም ሰብሳቢው በሚወስኑት ሌላ ቦታ ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፡፡

37.17. በሥራ ላይ ባሉ ሕጎችና ደንቦች መሠረት የማኅበሩን ካፒታል በቀጥታ የማይጨምሩ ሠነደ መዋዕለ ንዋዮችን ለገበያ ማቅረብ ላይ ውሳኔ የመስጠት ሥልጣን አለው፡፡ ይህም ሥልጣኑ ቦንዶችን፣ የዕዳ ሠነዶችን፣ ማስታወሻዎችን (ኖቶች) ወይም ሌሎች የዕዳ ሠነደ ሙዓለ ንዋዮችን እና ተዛማች ውሎችን (ዴሪቬቲቮች) ይጨምራል፤ ነገር ግን በእነዚህ ብቻ ሳይገደብ ሌሎች ስልጣኖች ይኖሩታል፡ ፡

37.18. የማኅበሩን ማንኛውም ሠነደ ሙዓለ ንዋይ የኢትዮጲያ ካፒታል ገበያ ባለሥልጣንንና የኢትዮጲያ ሠነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ጨምሮ በተቆጣጣሪ የመንግስት አካላት፣ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ (OTC) ዘንድ የሚመዘገቡበትን፣ ወይም ለሽይጭ የሚቀርቡበትን፣ ዝርዝር ጉዳዮችን በተመለከተ ለመቆጣጠር፣ ለመጀመርና ለመወሰን ሥልጣን አለው፡፡

37.19. የኢትዮጲያ ካፒታል ገበያ ባለሥልጣን፣ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ፣ ያልተማከሉ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያዎች ወይም ሌላ ማንኛውም አግባብነት ያለው ተቋም በሚያዝዘው መሠረት የካፒታል ገበያ መስፈርቶች፣ የማሳወቅ ግዴታዎች፣ የሪፖርት አቀራረብ ደረጃዎችና የኩባንያ አስተዳደር ግዴታዎች ቀጣይነት ባለው ሁኔታ እየተከበሩ መሆናቸው የሚያረጋግጥ ሥልጣን አለው፡፡

37.20. ቦርዱ አግባብ ባላቸው ሕጎች መሰረት ማህበሩ የሚያወጣቸውን ሰነደ መዓለ ንዋያትን ግዑዝ አልባ (dematerialization) ስለሚሆኑበት ሁኔታ የመወሰን፤ አግባብነት ባለው ሕግ እና ሕጉን በሚያስፈፅመው አካል የሚጠየቁ ሰነዶችን የማዘጋጀት፣ ሰነዶቹም ሥልጣን ባላቸው አካላት ዘንድ የሚመዘገቡበትን ሁኔታ የመወሰን እና ባለአክሲዮኖች እና የድርጅቱ አመራር አካላት ስለዚሁ ሂደት ተገቢውን ግንዛቤ እንዲኖራቸው ለማድረግ የሚያስችሉ ሥራዎችን በሙሉ የመሥራት ሥልጣን አለው፡፡

37.21. ቦርዱ ከዚህ በላይ የተሰጡትን ሥልጣኖቹን ተግባራዊ ለማድረግ እንዲችል የግብይት አማካሪ (transaction advisor) ፤ ገለልተኛ የውጭ የሕግ አማካሪ (exteranal legal advisor) እና ሌሎች አስፈላጊ ባለሙያዎችን እና አማካሪዎች የመቅጠር፣ የመለወጥ እና የማሰናበት/የማቋረጥ ሥልጣን አለው፡፡

37.22. የዳይሬክተሮች ቦርድ የራሱን የአሰራር ሥርዓት ደንብ ያወጣል፡፡

37.23. ከላይ የተዘረዘሩት እንደተጠበቁ ሆነው በዚህ መመስረቻ ጽሑፍ ለማህበሩ ሌላ አካል ተለይተው ካልተሰጡ በስተቀር ለማህበሩ የተሰጡ ስልጣን እና ተግባራትን ሙሉ የዳይሬክተሮች ቦርድ ያከናውናል፡፡

37.24. የዳይሬክተሮች ቦርድ እንደአስፈላጊነቱ ስልጣኑን ለአንድ ወይም ከአንድ ላይ ለሆኑ የቦርድ አባላት ወይም ለዋና ስራ አስፈጻሚው ውክልና መስጠት ይችላል፡፡

37.25. የዳይሬክተሮች ቦርድ በማህበሩ ውስጥ ካለ ወይም ከሌላ ከማንኛውም ሰው የሙያ ድጋፍ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

37.26. በጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ ወይም በሕግ ተለይተው የተሰጡ ሌሎች ስራዎች ያከናውናል፡፡

<u>አንቀጽ ሰላሳ ስምንት: የማህበሩ ዋና ሥራ አስፈጻሚ</u>

38.1. ማህበሩ በዳይሬክተሮች ቦርድ የሚሾም አንድ ዋና ስራ አስፈጻሚ ይኖረዋል፡፡

38.2. ዋና ሥራ አስፈጻሚው ተጠሪነቱ ለዳይሬክተሮች ቦርድ ሆኖ ደሞዝና ጥቅማጥቅሙ በዳይሬክተሮች ቦርድ ይወሰናል፡፡

38.3. ዋና ሥራ አስፈጻሚው ከዳይሬክተሮች ቦርድ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ፣ በዚህ መመሥረቻ ፅሁፍና አግባብ ባላቸው ህጎች መሠረት የማህበሩን አስተዳደር እና የዕለት ከዕለት ሥራ ያካሄዳል፡፡

38.4. ቀደም ሲል የተገለጸው ጠቅላላ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ሥራ አስፈጻሚው የሚከተሉት ስልጣን እና ተግባራት ይኖሩታል፡፡

38.4.1. የማህበሩን የዕለት ተዕለት ሥራ ይመራል፡፡ ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረግ ግንኙነት ማህበሩን ይወክላል፡፡

38.4.2. ማህበሩ ለተቋቋመበት ዓላማ ግብ መምታት ተገቢው ጥረት ያደርጋል፡፡

38.4.3. የማህበሩን አጠቃላይ እንቅስቃሴ ያቅዳል፣ ያስተባብራል፣ ይመራል፣ ያስተዳድራል፣ ይቆጣጠራል፡፡

38.4.4. የማህበሩን ስትራቴጂክ ዕቅድ፣ ዓመታዊ ዕቅድና በጀት ማዘጋጀት ለቦርድ አቅርቦ ማጸደቅ ተግባራዊ ያደርጋል፤

38.4.5. ትክክለኛ እና የተሟላ የሥራ ክንውን ሪፖርት በየሶስት ወሩ፣ በየሂሳብ ሪፖርት የዓመቱ ለዳይሬክተሮች ቦርድ ያቀርባል፤

38.4.6. ማህበሩን ከኪሳራ ከጥፋት፣ ከድንገተኛ አደጋና ከማናቸውም ዓይነት ዕዳ ለመጠበቅ የሚያስችል የመድን ዋስትና ከታወቀ የመድን ኩባንያ ወይም ከሰው ጋር ይዋዋላል፣

38.4.7. በህግ የተቀመጡ እና ለማህበሩ ስራ አስፈላጊ የሆኑ የአሰራር መመሪያዎችን፣ ማኑዋሎችንና የቁጥጥር ሥርዐቶችን በማጽደቅ ስራ ላይ ያውላል፤

38.4.8. ለማህበሩ ውጤታማ የውስጥ ቁጥጥር እና የአደጋ ተጋላጭነት ቁጥጥር ስርዐት ይዘረጋል፤

38.4.9. አስተማማኝ የኢንፎርሜሽን ሲስተም አዘጋጅቶ ለቦርድ ያቀርባል፤ ሲጸድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፤

38.4.10. የማህበሩን ድርጅታዊ መዋቅር በማዘጋጀት ዳይሬክተሮች ቦርድ ያጸድቃል፤ ተግባራዊ ያደርጋል፤

38.4.11. ቦርድ መሾም ካለባቸው ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች ውጪ ማህበሩ ድርጅታዊ መዋቅር መሠረት አስፈላጊ የሆኑ የስራ ኃላፊዎች እና ሰራተኞችን ይቀጥራል፣ ክፍያቸውን ይወስናል፣ በህግ አግባብ ያሰናብታል፣

38.4.12. የማህበሩን ምክትል ስራ አስፈጻሚዎች ሹመት ለዳይሬክተሮች ቦርድ ማቅረብ ያጸድቃል፤

38.4.13. ዳይሬክተሮች ቦርድ በተፈቀደው የአሰራር ሥርዓትና የሂሳብ አያያዝ ደንብ መሠረት ወጪዎችን ያፀድቃል፣ በህግ የታዘዙ የመጠባቂያ ሂሳቦችን ያቋቁማል፡፡

38.4.14. ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እና ከሀገር ውስጥ የፋይናንስ ተቋማት በማህበሩ ስም ብድር ይበደራል፣ የግምጃ ቤት ሰነዶችን እና ሌሎች ዕዳ ሰነዶችን ይገዛል፣ ይለውጣል ወይም ይሸጣል፤

38.4.15. በቼክ፣ የሚተላለፉ ሰነዶች፣ እንደ የሃዋላ ወረቀት ያሉ የንግድ ሠነዶችን ማውጣት፣ መፈረም፣ መቀበልና ማስተላለፍ፣

38.4.16. የማኅበሩን የባንክ ሒሳብ የሚያንቀሳቅሱ ፈራሚዎቸን ይመድባል፤

38.4.17. ግዥና ሽያጭን በተመለከተ ከሥሩ ለሚገኙት ሠራተኞች መመሪያ ይሰጣል፤

38.4.18. የማህበሩን ዓላማ ለማሳደግ በዳይሬክተሮች ቦርድ ሲፈቀድ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶችን ያቋቁማል፤ ይመራል፣ ይቆጣጠራል፣ አስፈላጊ ሲሆን እንዲዘጉ ያደርጋል፤

38.4.19. የሥራ መጓተትን የሚያስቀርና ትርፋማነትን የሚጨምር የተቀላጠፈ የውስጥ ቁጥጥር መዋቅርና አሠራር ይዘረጋል፡፡

38.4.20. የሠራተኛ ሕግና የማህበሩ መመስረቻ ጽሁፍ እንዲሁም የማህበሩ የስራ ደንብ በሚፈቅዱት መሠረት ሰራተኞች ላይ አስተዳደራዊ እርምጃዎችን ይወስዳል፡፡

38.4.21. ከመደበኛ የብድር ማስመለስ ጋር ተያያዥ የሆኑ የሚንቀሳቀሱ እና የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን ይገዛል፣ ይሸጣል፣ መያዣ ይሰጣል፣ ያስወግዳል፡፡

38.4.22. ከመደበኛ ብድር ማስመለስ ጋር ተያያዥ ከሆኑት ውጭ በዳይሬክተሮች ቦርድ ውሳኔ መሠረት የማህበሩን የሚንቀሳቀስ እና የማይንቀሳቀስ ንብረት ይገዛል፣ ይሸጣል፣ ያስወግዳል፡፡

38.4.23. ዳይሬክተሮች ቦርድ ውሳኔ መሠረት ከውጪ አገር የገንዘብ ተቋማት ጋር የሚፈጸሙ የብድር ወሎችን ይፈርማል፡፡

38.4.24. ማህበሩን ወክሎ ከሶስተኛ ወገን እና ከመንግስት አካላት ጋር ውል ይዋዋላል፤ ይፈራረማል፣

38.4.25. በማህበሩ ስም የሕንጻ፣ የተሽከርካሪ ወይም ሌላ ማናቸውም ንብረት ኪራይ ውል ይፈራረማል፤

38.4.26. ማህበሩ ስም ሀገር ውስጥና ውጭ ሀገር በሚገኙ የፋይንስ (የውጪ ምንዛሪ ጨምሮ) ሂሳብ ይከፍታል ያንቀሳቅሳል፣ ውጭ ሀገር ስለሚከፈቱት ሂሳቦች እና የገንዘብ ዓይነት ለቦርዱን ሪፖርት ያደርጋል፤

38.4.27. ቦርዱ ሲፈቅድ ዳይሬክተሮች ቦርድ ስብሰባ ላይ በመገኘት በውይይቱ ተሳታፊ ይሆናል፡፡ ድምፅ መስጠት ግን አይፈቀድለትም፡፡

38.4.28. የማህበሩን ጥቅም ለመጠበቅ ከማህበሩ ሠራተኞች ውጭ ጠበቃ ለማቆም ወኪሎች ለመሾም እንዲሁም ሌሎች ባለሞያዎች ለመቅጠርና ለማሰናበት ሥልጣን ይኖረዋል፣

38.4.29. በንግድ ህግ፣ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ ወይም በዳይሬክተሮች ቦርድ የተሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፤

38.4.30. ዋና ሥራ አስፈጻሚው እንደአስፈላጊነቱ ስልጣኑን ለአንድ ወይም ከአንድ ላይ ለሆኑ የማህበሩ ከፍተኛ ኃላፊዎች፣ ወይም ሰራተኞች ውክልና መስጠት ይችላል፡፡

<u>አንቀጽ ሰላሳ ዘጠኝ: የማህበሩ ፀሐፊ</u>

39.1. በማህበሩ ዋና ሥራ አስፈጻሚው አቅራቢነት ዳይሬክተሮች ቦርድ የሚሾም ጸሐፊ ይኖረዋል፡፡ የጸሀፊው ተጠሪነት ለማህበሩ ስራ አስኪያጅ ነው፡፡

39.2. ንግድ ህጉ እና ብሔራዊ ባንክ መመሪያ የተቀመጡት ተጨማሪ ግዴታዎች እንደተጠበቁ ሆነው የማህበሩ ጸሐፊ የሚከተሉት ስልጣን እና ተግባራት ይኖሩታል፡፡

39.2.1. የዳይሬክተሮች ቦርድ ፀሐፊ በመሆን ማገልገል፤

39.2.2. የማህበሩ ጠቅላላ ጉባዔዎች ተቃራኒ ውሳኔ ከሌለ በስተቀር የጠቅላላ ጉባዔው ጸሐፊ መሆን ማገልገል፤

39.2.3. የማህበሩን መረጃዎችና መዛግብት የማደራጀትና የመያዝ፤

39.2.4. ለብሔራዊ ባንክ እና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት ሪፖርቶችንና ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችን በወቅቱ መስጠት፤

39.2.5. የጠቅላላ ጉባኤ ተሳታፊዎች መመዝገቢያ ሰነድ በስብሰባው መጀመሪያ ላይ በጉባኤው በአካል የተገኙ ባለአክስዮኖች ወይም ወኪሎቻቸው የፈረሙበት መሆኑን ያረጋግጣል፣

39.2.6. ለባለአክሲዮኖች እና ለሶስተኛ ወገኖች መረጃ መስጠት፤

39.2.7. የባአክሲዮኖችን እና የቦርድ አባላትን ስብሰባዎች ማዘጋጀት፣

39.2.8. ለቦርድ ስብሰባ የሚሆኑ አጀንዳዎችን እና አስፈላጊ ሰነዶችን ለቦርድ አባላት ማሳወቅ፤

39.2.9. የጠቅላላ ጉባዔ እና የቦርድ ቃለ ጉባዔዎችን ማዘጋጀትና አደራጅቶ መያዝ፤

39.2.10. የዳይሬክተሮች ቦርድ ውሳኔዎችን ለማህበሩ ማኔጅመንት በጽሁፍ ማሳወቅ፤

39.2.11. ዳይሬክተሮች ቦርድ እና ዋና ሥራ አስፈጻሚው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ማከናወን፡

<u>አንቀጽ አርባ: ኦዲተሮች</u>

40.1. ማህበሩ አንድ ወይም ከአንድ ላይ ነጻና ገለልተኛ ኦዲተሮች ይኖሩታል፡፡ የኦዲተር ወይም ኦዲተሮች ሹመት እና የስራ ዋጋ ዳይሬክተሮች ቦርድ አቅራቢነት መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ መጽደቅ ይኖርታል፡፡

40.2. የኦዲተሮች የሥራ ዘመን ሦስት ዓመት ነው፡፡ ሆኖም መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤው ማናቸውም ጊዜ ኦዲተሮችን ሊያነሳ ይችላል፡፡

40.3. ኦዲተር ሆኖ ለመሾም የሚያስፈልጉ መስፈርቶችን በተመለከተ በንግድ ህግ አንቀጽ 345 እና ብሔራዊ ባንክ መመሪያ ላይ በተቀመጡት መመዘኛ መስፈርቶች መሰረት ይሆናል፡፡

40.4. በንግድ ህጉ እና ብሔራዊ ባንክ መመሪያ የተገለጸው እንደተጠቀ ሆኖ የማህበሩ ኦዲተር ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩት ሥልጣንና ግዴታዎች ይኖሩታል፡፡

40.4.1. የማህበሩን ንብረት ዝርዝር መዝገብ፣ የሂሳብ ሚዛንና የትርፍና ኪሳራ መግለጫ እና ሌሎች የሂሳብ ሰነዶችን ትክክለኛነት መመርመር እና ማረጋገጥ፤

40.4.2. ተቀባይነት ያላቸውን የሒሳብ አያያዝ መርሆች መሰረት ማድረግ መስራት፤

40.4.3. የሙያ ሥራ ምስጢር የመጠበቅ፤

40.4.4. ትክክለኛ መረጃ የመስጠት፤

40.4.5. የዳይሬክተሮች ቦርድ ሪፖርት የማህበሩን ትክክለኛ ገፅታ የሚያሳይ መሆኑን ማረጋገጥ፤

40.4.6. ሥራውን ለማከናወን አስፈላጊ ነው ተብሎ የሚያምንበትን መዝገብ፣ ሰነድ፣ ቃለ ጉባኤ እና ሌሎች መረጃዎችን ባለበት ማየት መመርመር፤

40.4.7. ንግድ ህጉ አንቀጽ 349 መሠረት ለማህበሩ ዓመታዊ ጠቅላላ ጉባዔ ሪፖርት ማቅረብ፤

40.4.8. የማህበሩን የፋይናንስ እና ስራ አመራር ተመለከተ ማንኛውም ጊዜ አስቸኳይ ምርመራ ማድረግ፤

40.4.9. ህገ ወጥ እና ትክክለኛ ያልሆኑ አሰራሮችን ለጠቅላላ ጉባዔ ወይም ለቦርድ ማሳወቅ፤

40.4.10. ሌሎች በሕግ የተደነገጉ ወይም ጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔ መሰረት የሚሰጡ ግዴታዎችን መፈፀም፡

40.5. የኦዲተሮች ኃላፊነት ሥልጣንና ተጠያቂነት በንግድ ሕግ ቁጥር 354 እና ብሔራዊ ባንክ መመሪያዎች ተመለከተው መሠረት ይሆናል፡፡

ምዕራፍ አራት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

አንቀጽ አርባ አንድ: ስለ ማህበሩ ዓመታዊ ሪፖርት

ማህበሩ ዓመታዊ የፋይናንስ ሪፖርቱንና በሕግ የሚጠበቁ ሪፖርቶችን ሕጋዊ ማስታወቂያ ማውጣት በሚችሉ በሀገሪቱ በሰፊው የሚዘወተሩ ጋዜጦች እና ማህበሩ ድህረገጽ ላይ ያወጣል፡፡

አንቀጽ አርባ ሁለት: የማህበሩ ሂሳብ ዓመት

የማህበሩ ሂሳብ ዓመት እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር ከጁላይ 1 እስከ ሚቀጥለው ጁን 30 ቀን ነው፡፡

አንቀጽ አርባ ሶስት: ሕጋዊ የመጠባቂያ ገንዘብ

43.1. በንግድ ሕጉ አንቀፅ 434(1) መሠረት ከማኅበሩ የተጣራ ትርፍ አምስት በመቶ (5%) በየዓመቱ በሕግ ወደተወሰነው መጠባበቂያ ገንዘብ መዛወር ይኖርበታል፤ ሆኖም ወደ መጠባበቂያው የተዛወረው ገንዘብ መጠን የማኅበሩን ዋና ገንዘብ አምስት በመቶ (5%) ላይ ሲደርስ የማዛወሩ ተግባር አስገዳጅነት ይቀራል፡፡

43.2. በማንኛውም ምክንያት በሕግ የተወሰነው የመጠባበቂያ ገንዘብ በዚህ መመስረቻ ጽሑፍ በንዑስ አንቀጽ (43.1) ከተመለከተው መጠን ዝቅ ያለ እንደሆነ ወደዚያው መጠን እንዲመለስ ገንዘብ የማዛወር ግዴታ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

43.3. በንግድ ሕጉ አንቀፅ 434 ንዑስ አንቀጽ (2) እና በዚህ መመስረቻ ጽሑፍ ንዑስ አንቀጽ (43.1) እና (43.2) የተደነገጉት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነዉ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ የማኅበሩን መጠባበቂያ ገንዘብ በሙሉ ወይም በከፊል ወደ ዋና ገንዘብ በማዛወር የማኅበሩን ዋና ገንዘብ ማሳደግ ይችላል፤ ሆኖም በሕግ የተወሰነው የመጠባበቂያ ገንዘብ ወደ ማኅበሩ ዋና ገንዘብ እንዲገባ ከተደረገ

የቀድሞው በሕግ የተወሰነው መጠባበቂያ ገንዘብ እንደገና እስኪሟላ ድረስ ለባለአክስዮኖች ማንኛውንም ዓይነት ክፍፍል ማድረግ አይቻልም፡፡

43.4. ከዳይሬክተሮች ቦርድ ወይም ከኦዲተር ሃሳብ የቀረበለት እንደሆነ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤው ተጨማሪ ወይም አማራጭ የመጠባቂያ ገንዘብ እንዲኖር መወሰን ይችላል፡፡

አንቀጽ አርባ አራት: የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት

44.1. የማኅበሩ የሒሳብ መዛግብትና የንብረት ሰነዶች በሕግና በንግድ ስራ ተቀባይነት ባገኙ ደንቦችና መርሆዎች መሠረት ይያዛሉ፡፡

44.2. ማኅበሩ በእያንዳንዱ የሒሣብ ዓመት መዝጊያ የሀብቱንና የዕዳውን ዝርዝር የሚመለከቱ ሰነዶች ማዘጋጀት ይኖርበታል፣

44.3. የዳይሬክተሮች ቦርድ የማኅበሩን የሒሳብ ሚዛን መግለጫ፣ የትርፍ እና ኪሣራ መግለጫ እንዲሁም ባለፈው የሒሳብ ዓመት የነበረውን የማኅበሩን ሁኔታ እና እንቅስቃሴ በተመለከተ ሪፖርት ማዘጋጀት አለበት፤

44.4. የማኅበሩ የሂሣብ ሪፖርት የኪሣራውንና የትርፋን ሂሣብ የሚገልጽ ዝርዝር የያዘና የቦርዱ አባላት፣ ዋና ሥራ አስፈፃሚዉና ኦዲተሮች የሚያገኙትን የሥራ ዋጋ በትክክል የሚያመላክት፣ስለ ትርፍ ክፍያም የቀረበ ኃሳብ ካለ ስለአከፋፈሉ በግልጽ የሚያመለክት መሆን ይኖርበታል፡፡

አንቀጽ አርባ አምስት: ስለ ትርፍ አደላደልና አከፋፈል

45.1. የማህበሩ ትርፍ ክፍፍል የሚደረገው ከተጣራው የማህበሩ ትርፍ ላይ ያለፉ ዓመታት ኪሳራዎች፣ ሕጋዊ መጠባቂያዎች፣ የትርፍ ክፍፍል ግብር እና ሌሎች መቀነስ ያለባቸው ሂሳቦች ከተቀነሱ በኋላ ነው፡፡

45.2. የባለአክሲዮኖች የትርፍ መጠን የሚሰላው ማህበሩ ውስጥ የተከፈለ ካፒታል መጠንና የተከፈለትን ካፒታል ሂሳብ ዓመቱ የተከፈለት ጊዜ ግምት ውስጥ ማስገባት ነው፡፡

45.3. የትርፍ ክፍፍል መቼና እንዴት መፈፀም እንዳለበት ዳይሬክተሮች ቦርድ የውሳኔ ሀሳብ አቅራቢነት ዓመታዊ ጠቅላላ ጉባዔ ይወሰናል፡፡

አንቀጽ አርባ ስድስት: ስለማህበሩ መፍረስ እና ሂሳብ ማጣራት

ማህበሩ በሕግ ወይም ባለአክሲዮኖች ውሳኔ በንግድ ህጉ እና አነስተኛ ፋይናንስ ስራ አዋጅ ቁጥር 1360/2017 መሠረት ብሔራዊ ባንክ ሲፈቅድ ሊፈርስ ይችላል፡፡ አፈፃፀሙም አዋጁ ተመለከተው መሠረት ይሆናል፡፡

46.1. ማኅበሩ እንዲፈርስ የወሰነው ጠቅላላ ጉባኤ ከሶስት የማያንሱ ሒሳብ አጣሪዎችን ይሾማል፡፡

46.2. ጠቅላላ ጉባኤው የማኅበሩን ባለአክስዮኖች በሒሳብ አጣሪነት ለመሾም ይችላል፡፡

46.3. ማኅበሩ እንዲፈርስ የወሰነው ጠቅላላ ጉባኤ የሒሳብ አጣሪዎችን የሥራ ዋጋ ይወስናል፡፡

46.4. ከዕዳ ክፍያ የሚተርፈው የተጣራ ሒሳብ በተከፈሉ አክስዮኖች መጠን ለባለአክስዮኖች ይከፋፈላል፡፡

አንቀጽ አርባ ሰባት: ማህበሩ የተቋቋመት ጊዜ

ማህበሩ የተቋቋመው ላልተወሰነ ጊዜ ነው፡፡

አንቀፅ አርባ ስምንት፡ የግልግል ዳኞች

በማኅበሩና በአባላቱ መካከል አለመግባባት ቢፈጠር ሁለቱም ወገኖች በሚመርጧቸው የግልግል ዳኞች ጉዳያቸው እልባት እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡ ሆኖም አንደኛው ወገን ለመምረጥ ካልተስማማ የግልግል ዳኞችን ፍ/ቤት ሊመርጥላቸው ይችላል፡፡

አንቀጽ አርባ ዘጠኝ: መመስረቻ ጽሁፍ ስለማሻሻልና ተፈጻሚነት

49.1. መመስረቻ ፅሑፉ በግልፅ ያልተካተቱ ጉዳዮች ንግድ ሕጉ እና አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሠረት ይወሰናሉ፡፡

49.2. ይህ መመስረቻ ጽሁፍ የሚሻሻለው በአስቸኳይ ጉባኤ ነው፡፡

49.3. ይህ መመስረቻ ጽሁፍ ተፈፃሚነት የሚያገኘው በጠቅላላ ጉባኤ ከፀደቀ በኋላ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ተፈቅዶ ሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ኤጀንሲ ሲመዘገብ ነው፡፡